# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 118 ነሃሴ 13 ቀን 2002 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!፡”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## የአውራምባ ታይምስ ጽ/ቤት ባልታወቁ ግለሰቦች ጥቃት ተፈጸመበት፤ በጥቃቱ የጽ/ቤቱ የጥበቃ ሰራተኛ ክፉኛ የተጎዳ መሆኑ ተገለጸ

ነሃሴ 11 ቀን 2002 ዓ.ም ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ላይ ሲሆን ማንነታቸው ያልታወቁ ግለሰቦች ወደ ጽ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ለመዝለቅ መሞከራቸውን በዚሁ እለትም ይህ ሙከራ ከመደረጉ ስድስት ሰአታት ቀደም ብሎ ግርግር ተፈጥሮ እንደነበርና ይህም ግርግር ሌሊት ላይ ከተፈጸመው ጥቃት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንደነበረው የአይን እማኞችን በመጥቀስ ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርት አስታውቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዚሁ እለት እነኚህ ማንነታቸው ያልታወቁት ግለሰቦች የተፈጠረውን ችግር በሰላም ለመፍታት ያደረገውን ጥረት ተከትሎ የአውራምባ ታይምስ ምክትል ኤዲቶር የሆነውን ግዛው ለገሰን ማስፈራሪያና ወቀሳም እንደሰነዘሩበት በወቅቱ ችግሩ ሲከሰት ያዩ እማኞች እንደገለጹለት ዘጋቢያችን ገልጿል። በሌላም በኩል ከአውራምባ ታይምስ ጽ/ቤት ችግሩን አስመልክቶ ህጉ በሚያዝዘው መሰረት በወቅቱ ለሚመለከተው የፖሊስ ጽ/ቤት ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም የተሰጠው ምላሽ አሳዛኝ እንደሆነበት የአውራምባ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አንድ መቶ የአለም አገራትን የኑሮ ሁኔታ ያነፃፀረ አዲስ ሪፖርት ኢትዮጵያን 94ኛ ደረጃ ላይ አስቀመጠ

ታዋቂው የአሜሪካ ጋዜጣ ኒውስዊክ “ዛሬ ብትወለድ፥ የትኛው አገር በጤና፣ በደህንነት፣ በብልጽግና፣ እና በእድገት የተሞላ ኑሮ እንዲኖርህ ከፍተኛውን እድል ይሰጥሃል?” የሚለውን ጥያቄ ይዞ በመነሳት መቶ አገሮችን አነፃጽሮ ደረጃን ያወጣ ሲሆን ከነዚህ መቶ አገሮች ውስጥም ኢትዮጵያን 94ኛ ደረጃ ላይ ያስቀመጣት መሆኑን ለማወቅ ተቿሏል።

ኒውስዊክ ትምህርትን፣ ጤናን፣ የኑሮ ጥራት ደረጃን፣ የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትን፣ እና የፖለቲካ ሁኔታን እንደማነፃጸሪያ ነጥቦች የተጠቀመ ሲሆን ለምሳሌ የኑሮ ጥራት ደረጃን ለመመዘን ከተጠቀመባቸው ቁልፎች ውስጥ አንዱ “በቀን ከሁለት ዶላር በታች” የሚያገኙ ዜጎች ቁጥር ሲሆን፤ ከዛ አኳያ ኢትዮጵያ ውስጥ 77.57% የሚሆነው ህዝብ ያንን ገቢ እንደሚያገኝ አስቀምጧል። ይህ የኒውስዊክ ሪፖርት አገራቱን ለማነፃጸር የተጠቀመው መረጃ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር 2008 እና 2009ን የሚሸፍን መሆኑ ታውቋል።

በእንግሊዝ አገር የሚገኘው ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ከተበባሩት መንግስታት ጋር በመተባበር ከአንድ ወር በፊት ባወጣው ሪፖርት ላይ “መልታይ ዳይሜንሽናል ፑቨርቲ ኢንዴክስ” የተባለ ዘርፈ ብዙ የድህነት መመዘኛ በመጠቀም የአለም አገራትን አወድድሮ፤ ኢትዮጵያ ከአፍሪካዊቷ ኒጀር ቀጥላ ሁለተኛዋ የአለም ደሃ አገር እንደሆነች እና 90% የሚሆኑት ዜጎቿም በድህነት እንደሚማቅቁ መግለጹን መዘገባችን ይታወሳል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ሊቀላቀሉት ፈቃደኛ ባልሆኑ ዜጎች ላይ የጥቃት እርምጃዎች እየወሰደ መሆኑ ታወቀ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ፣ “አንወይንም” ወይም ገዢውን ፓርቲ አንቀላቀልም ባሉ ዜጎች ላይ የበቀል እርምጃዎችን እየወሰደ መሆኑን ሰሞኑን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዘገባ አሳይቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ እንደላከው ዘገባ፥ አገዛዙ እንዲቀላቀሉት ጫና ተደርጎባቸው ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎችን በቁጥጥሩ ስር ያሉትን ፍርድ ቤቶች በመጠቀም ያለ በቂ ክስ እና ማስረጃ ወደ ዘብጥያ እያስወረወረ ነው።

በዚህ አኳኋን ሰሞኑን በደቡብ ክልል በአርባ ምንጭ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሰራተኞች የሆኑ አምስት ዜጎች የሁለት አመት እስራት በግፍ እንደተፈረደባቸው ሪፖርተራችን ምንጮቹን ጠቅሶ ዘግቧል። እንደ ምንጮቹ ዘገባ ግለሰቦቹ በማህበረሰባቸው ውስጥ ያላቸውን ተሰሚነት ለገዢው ፓርቲ ጥቅም እንዲያውሉ የወያኔ ካድሬዎች ሲያደርጉባቸው የቆዩትን ጫና አልቀበል ብለዋል።

ላለፉት አምስት አመታት የወያኔ አገዛዝ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን በጉቦ ወይም በማስፈራራት አባል ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል።

## በአዲስ አበባ ‘ያለ ጉቦ ምንም መስራት የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል’ ሲሉ ዜጎች አማረሩ

በአዲስ አበባ ከተማ ሙስና እጅግ መስፋፋቱን ሰሞኑን ከመዲናይቱ የደረሰን ዘገባ አሳይቷል።

አንዳንድ ነዋሪዎች “ጉቦ ሳይሰጥ እርምጃ እንኳ መራመድ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል” ሲሉ ለግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ስሞታቸውን አሰምተዋል። ዘጋቢያችን ያናገራቸውና በቤቶቻቸው ላይ ተጨማሪ ግንባታ ለመስራት ፈልገው ፈቃድ ለመጠየቅ ወደሚመለከተው የአስተዳደር አካል የሄዱ ዜጎች፤ በግልጽ ጉቦ እንደተጠየቁ ተናግረዋል።

የወያኔ ሹመኞች የሆኑት የአስተዳደር ሰራተኞች እርስበርስ ተቧድነው እንደሚሰሩ እና ያገኙትን ጉቦም እንደሚካፈሉ ለማወቅ ተችሏል። የደረሰባቸውን ግፍ ለዘጋቢያችን ካካፈሉት ውስጥ አንዱ ግለሰብ፣ አንድ የአስተዳደር ሰራተኛ የሆነ የወያኔ ካድሬ፣ “ይቺማ ለማን ተሰጥታ ለማን ትተርፋለች” በማለት የተሰጠው ጉቦ ትንሽ መሆኑን እና ለሱና ለተባባሪዎቹ እንደማይበቃ በግልጽ አስረድቷል።

የወያኔ አገዛዝ በተለይም በ1997ቱ ምርጫ ከደረሰበት ሽንፈት በኋላ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አባላትን ለማግበስበስ ሲል ከተጠቀማቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ ሙስናን መፍቀድ እና ማበረታታት እንደሆነ ይታወቃል።

## የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያሉ ኤርትራውያን ስደተኞችን ለፖለቲካ ፍጆታ እየተጠቀመ ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ኤርትራውያን ስደተኞችን አስመልክቶ ባወጣው መመሪያ ወደ 36 ሺ ይጠጋሉ ያላቸወን በፈለጉት ያገሪቱ ክፍሎች ተዘዋውረው መሥራትና መኖር ይችላሉ ማለቱ ብዙ ሰዎችን እያነጋገረ መሆኑን የአዲስ አበባው ዘጋቢያችን ከስፍራው ከላከልን ዜና ለመረዳት ተችሎአል።

ከሁለቱም ወገን ወደ መቶ ሺ ለሚጠጋ የወንድማማቾች ህይወት ህልፈት ምክንያት በነበረው ኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት “የዓይኑ ቀለም ያላማረንን ሁሉ የማባረር መብት አለን “ በሚል ፍጹም ዘረኛ አመለካከት ለ ዓመታት ያካበቱትን ሃብት ንብረት በህገ ወጥ መነገድ ዘርፎ ያባረረው ተመሳሳይ ዜግነት አላቸው የሚባሉትን ሰዎች እንደነበር የሚያስታውሱ ወገኖች ወያኔ ይህንን የሚያደርገው ለስልጣን ያበቃውን የአሁኑን የኤርትራ አስተዳደር ተቀናቃኞችን ለማበረታታት እንደሆነ ይናገራሉ።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ያናገራቸው አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፥ ኢትዮጵያውያን እራሳቸው እንደፈለጉ መንቀሳቀስ በማይችሉበት አገር ይህ መብት ለኤርትራውያን ተሰጠ መባሉ የማይመስልና ርካሽ የሆነ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ተብሎ የተቀነባበረ የተለመደው የወያኔ ቅጥፈት ነው ብለዋል። ወያኔ እንደ ኦሮሚያ ባሉ ክልሎች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የገቢዎች ሚንስቴር ካቀድኩት በላይ ታክስ ሰበሰብኩ ማለቱ ተሰማ

በአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ እንደተፈለገ የሚሽከረከረው የገቢዎች ሚንስቴር በዓመቱ ታቅዶ ከነበረው በላይ ከታክስ ገቢ አገኘሁ ካለ በኋላ ካቀድኩት በላይ ታክስ የሰበሰብኩት ታክስ ከፋዩ ሕብረተሰብ ታክስ የመክፈል አስፈላጊነት ግንዛቤው በመጨመሩ፣ ህብረተሰቡን ታክስ እንዲከፍል ማንቀሳቀስ በመቻላችንና ሕብረተሰቡ ለህጉ ታማኝ በመሆኑ እንደሆነ ገልጿል። ከዚህም በተጨማሪ ለዚህ ታክስ ገቢ ከፍ ማለት አስተዋጽኦ ያደረገው ከታክስ ጋር በተያያዘ ወደ ፍርድ ቤት የወሰድናቸውን ክሶች በሙሉ ማሸነፍ በመቻላችን ነው ብሏል።

ይሁን እንጂ የታክስ አሰባሰቡን አስመልክቶ አስተያየታቸውን ለግንቦት ሰባት ዘጋቢ የሰጡ በንግድ ስራው ዘርፍ የተሰማሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እውነታው ፍጹም ከዚህ የተለየ ነው፤ የንግዱ ህብረተሰብ እንዲከፍል በሚጠየቀው የታክስ መጠን እጂግ በጣም እያማረረ መሆኑንና ማናቸውም የንግድ ድርጅት ትንንሽ ሻይ ቤቶች እንኳን ሳይቀሩ ተጨማሪ እሴት ታክስ ለመክፈል እንዲመዘገቡ እንደተገደዱም መግለጻቸውን ዘጋቢያችን ገልጾልናል።

ከዚሁ ጋር በማያያዝም የወያኔው አገዛዝ በተለይም በመካከለኛ የገቢ አቅም ላይ የሚገኘውን የንግድ ህብረተሰብ ክፍል በተለያዩ መንገዶች የሚፈጽምበት ግፍና በርካቶችም ከንግድ ስራ ውጪ እንዲሆኑ ማድረጉ ሳያንሰው አሁንም ፍጹም ፍትሃዊነት በጎደለው አሰራር ታክስ የመሰብሰብ ተግባሩን መቀጠሉ ምን ያህል ህብረተሰቡን እንደናቀና ምንም አያመጡም በማለት መተበቱን ያሳየናል ብለዋል። ሌላው አስተያየት ሰጪ ከመርካቶ በርግጥ ማንም ሰው ከሚያገኘው ገቢ ለመንግስት ተገቢ በሆነ መልኩ ታክስ መክፈል እንዳለበት ብናምንም ወያኔ እያደረገው ያለው አሰራር ግን በፍጹም ከዚህ የወጣ ነው በማለት በምሬት ገልጸዋል። በመቀጠልም እንዲህ አይነቱ ወያኔዎች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆኖ ልጆቹን ለማቆየት እየደከመ ያለውን (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# ርእሰ አንቀጽ

## ለመለስ የውሸት ድርድር ጥሪ ጆሮ የሚሰጥ የለም!!!

ሰሞኑን መለስ ዜናዊ ስለልዩ ልዩ ጉዳዮች በቀባጠረበት ጋዜጣዊ መግለጫ ከግንቦት 7 ጋር ሊኖር ስለሚችል ድርድርም ጥቂት ዓረፍተ ነገሮችን ተናግሯል። መለስ እንዲህ ጊዜ እየጠበቀ በሚወረውራቸው ዓረፍተ ነገሮች አዲስ አጀንዳ እየሰጠ ኢትዮጵያዊያንን ከትግል ማዘናጋት ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ተጠቅሞበት ውጤታማ የሆነበት ስልት እንደሆነ እናውቃለን። አሁንም ይህንን ሲወረውር ተመሳሳይ ውጤት እንደሚያስገኝለት ተስፋ በማድረግ እንደሆነ መገመት ይቻላል። ጠያቂው "ኢትዮ ቻናል" የተባለው አስመሳይ ጋዜጣ መሆኑም የድርድሩ ጉዳይ ሳይታሰብበት በነገር መሃል የመጣ ላለመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

ሆኖም ጊዜው ተቀይሯል። መለስን ማመን ብቻ ሳይሆን ከወያኔ ጋር ስለሚደረግ "ድርድር" "ብልህነት" ማውጠንጠን ቂልነት መሆኑ ሕዝባችን ተረድቷል። በዚህም ምክንያት ለአሁኑ የመለስ ንግግር ጆሮውን የሚሰጥ አዕምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብለን ባንገምትም አጋጣሚውን በመጠቀም ከወያኔ ጋር ሊኖር ስለሚችል "ድርድር" የንቅናቄዓችንን አቋም በድጋሚ ማሳወቅ ይጠቅማል በሚል ለመለስ የውሸት ጥሪ የንቅናቄያችንን እውነተኛ ምላሽ እንሰጣለን።

እንደሚታወቀው በወያኔ ባህርይ ምክንያት ሁሉንም ዓይነት የትግል ስልቶች እንደአመቺነታቸው ለመጠቀም ቆርጠን ተነስተን ተግባር ውስጥ ገብተናል። ይህንን የተለያዩ የትግል ስልቶች ኅብር "ሁለገብ የትግል ስልት" ብለነዋል። ሁለገብ የትግል ስልት የመረጥነው ወያኔ "ሰላማዊ" ብሎ በሚጠራው የባርነት መንገድ ለውጥ ማምጣት እንደማይቻል ሞክረን ካረጋገጥን በኋላ ነው። የወያኔን ባህርይ የሚመጥን የትግል ስልት ሁለገብ መሆን እንደሚኖርበት ሕዝባችንም በማያሻማ ሁኔታ የተረዳበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በንቅናቄዓችን መርሃ ግብር በተራ ቁጥር 6 ላይ በግልጽ እንደሰፈረው ሁለገብ የትግል ስልት "ልዩነቶችን በውይይት፣ በድርድርና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት በየወቅቱ ለሚፈጠሩ እውነተኛ እድሎች በሩን የማይዘጋ" ነው። እንዲያውም ግንቦት 7 ለእውነተኛ ድርድር ቅድሚያ እንደሚሰጥ በዚሁ ሰነድ ላይ በሚገባ አብራርቷል።

ይሁን እንጂ መዘንጋት የሌለበት አንድ ዓቢይ ነጥብ አለ። የድርድሮች ሁሉ እስትራቴጂያዊ ግብ የወያኔን ዘረኛ አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጨረሻው አምባገነን በማድረግ የመንግሥት ሥልጣን በሕዝብ ነፃ ምርጫ ብቻ የሚያዝበትን ሥርዓት መገንባት ነው። ስለሆነም ከወያኔም ጋር የሚደረገው ድርድር ወደዚያ ሥርዓት የሚያቀርበን ሊሆን ይገባል። በሌላ አገላለጽ ከወያኔ ጋር የሚደረግ "ድርድር" በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የወያኔን ሥልጣን ማብቃትን ማብሰሪያ ነው መሆን የሚችለው። ወያኔ ተገዶ ካልሆነ በስተቀር እንዲህ ዓይነቱን ድርድር በመልካም ፈቃዱ ያደርገዋል ተብሎ አይጠበቅም። ስለሆነም የሰሞኑ የእንደራደር ጥሪም ከተለመዱ የመለስ ፓለቲካዊ ጅምናስቲኮች አንዱ ነው፤ ሌላ ምስጢር የለውም።

መለስ በዚህ ቃለ መጠይቁ ውስጥ "ተደራዳሪ" ወገኖች ህገመንግሥቱንና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን ማክበርና ማስከበር እንዳለባቸው ተናግሯል። ህግ አለ የሚባለው በሥራ ላይ ሲውል ነው። እኛ እንደምናውቀው ወያኔ የሚመራበት አንዳችም ህግ የለም። ህግ ሳይኖር ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ሊኖር አይችልም። ለወያኔ መለስ ህግ ነው፤ መለስ ህገመግሥትም ነው። እኛ ለዚህ ህግና ህገመንግሥት አንገዛም!!!

መለስ መለወጥ ከፈለገ የራሱ ድርጅት ጽፎና ጠርዞ ላስቀመጠው፤ ሆኖም እስከዛሬ ሥራ ላይ ውሎ ለማያውቀው "ህገመንግሥት" ብሎ ለሚጠራው ድንጋጌ ራሱን ተገዢ ያድርግ። በርካታ ጉድለቶች ቢኖሩበትም "ህገመንግሥት" ተብሎ የሚወደሰው ድርሳን ተግባራዊ ሆኖ ቢሆን ኖሮ አገራችን ዛሬ በምትገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ባልተገኘችም ነበር።

በዚሁ ቃለ መጠይቅ መለስ "ህገመንግሥቱን ከተቀበለና በሰላም ለመታገል ከፈቀደ ማንኛውም ቡድንም ሆነ ግለሰብ ጋር ለመደራደር ዝግጁ ነን" አለ። ይህን የተናገረው በዚህ "ላም አለኝ - በሰማይ" ዓይነቱ ባዶ ተስፋ የሚታለሉ ጥቂት ቡድኖች፤ ያም ባይሆን ግለሰቦችን አገኛለሁ ብሎ ይሆናል። "ላም አለኝ በሰማይ ..." ከኢኮኖሚው አልፎ ፓለቲካም ውስጥ እየገባ መሆኑን ልብ ይሏል። የሕዝባችን መጎሳቆል በዓይኖቻችን እያየንም ቢሆን የ11 በመቶ ዓመታዊ የኢኮኖሚ እድገት "ሰማይ ላይ ካለች ላሙ" እንደሚያልብ በተደጋጋሚ ሲናገር ጥቂቶቻችን ግራ በመጋባታችን የልብ ልብ ተሰምቶት ቁጥሩን ወደ 15 በመቶ ማሳደጉን ያስተዋለ ሰው፤ መለስ ነገ "እንደኔ ለአገር አንድነት የቆመ"፤ "እንደኔ ልቡ በአገር ፍቅር የነደደ"፤ "እንደኔ ለአገር መስዋዕት የሆነ የለም" ሊለን መዘጋጀቱን ይረዳል። መለስ እንዲህ የእኛን ድክመቶች እየተጠቀመ ኢትዮጵያዊያንን የመበተንና የራሱን ተክለ ሰውነት የመገንባት ሥራ እየሠራ ነው።

በግንቦት 7 እምነት የኢትዮጵያ ጉዳይ የግለሰብ ቀርቶ የአንድ የፓለቲካ ፓርቲ ጉዳይ መሆኑ አክትሟል። እንደድሮው "የኢትዮጵያ ጉዳይ ከኔ በላይ ላሳር" የሚል ፓርቲም ሆነ ቡድን ዛሬ ቦታ የለውም። የኢትዮጵያ ጉዳይ በፀረ-ወያኔ የትግል ጎራ ያለነውን ሁሉ በጋራ የሚመለከት በመሆኑ ማንም በግል ተነስቶ ከወያኔ ጋር ልደራደር ቢል ራሱን ከማቅለል በስተቀር የሚያመጣው ፋይዳ የለም። የተናጠል ትግል እና የተናጠል ውሳኔ ወቅት አልፏል። ይህ ሃቅ ዘግይቶም ቢሆን እየገባን ነው። የዚህ ግንዛቤ መሠረት እየያዘ መምጣት ሊሆን ይችላል ይህን የመጨረሻውን የመበተኛ ሙከራ ለማድረግ መለስን ያነሳሳው።

ሁሌም ለእውነተኛ ድርድር አክብሮት ያለን ቢሆንም ልማደኛ ዋሾ እና ቃለአባይ መሆኑ በተደጋጋሚ ያስመሰከረውን የመለስ ዜናዊን ጥሪ የሚሰማ ጆሮ የለንም።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ለጋዜጠኞች የሰጠው ቃለመጠይቅ የተለመደና ቅጥፈት የተሞላበት ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ገለጹ

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ጠብመንጃ ካነሱና ከሌሎችም ያኮረፉ ድርጂቶችም ሆነ ግለሰቦች ጋር እደራደራለሁ ከማለት አንስቶ በመጪው አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በፍጹም በድህነት ስሟ አትጠራም በማለት ለጋዜጠኞች የሰጠውን ቃለመጠይቅ አስመልክቶ በርካታ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች የተለመደና ቅጥፈት የተሞላበት ንግግር ነው በማለትና በማጣጣል አስተያየታቸውን የሰጡት መሆኑን ዘጋቢያችን ከላከልን ዘገባ ለመረዳት ችለናል።

ዘጋቢያችን በተለያዩ ክፍለ ከተሞች በመዘዋወር ያነጋገራቸው ነዋሪዎች በሰጡት አስተያየት ይህ የአሁኑ የመለስ ንግግር አዲስ ያልሆነና ስብእናውን የበለጠ በማጉላት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እያላገጠ ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ያሉ ሲሆን ከዚህ ባለፈ መልኩ ግን የምእራቡን ዓለም ድጋፍ ለማግኘት ሲል የተጠቀመበት ማጭበርበሪያ ነው ብለዋል። ነዋሪዎቹ በተለይም መለስ በመጪው አምስት ዓመታት ውስጥ ሃገሪቱ ምንም የምግብ ርዳታ ከማትጠይቅበት ደረጃ ላይ አደርሳታለሁ፤ የምግብ ዋስትና ሙሉ በሙሉ ይረጋገጣል ብሎ መናገሩ ፍጹም የማያሳፍረውና ከ15 አመታት በፊት ተመሳሳይ ቃል መግባቱንና እንኳን እንደተናገረው ሊሆን ችግራችን ከነበረበት ሁኔታ ወደ ከፋ ደረጃ መሸጋገሩን የዘነጋ ነው ብለውታል።

እነኚህ አስተያየት ሰጪዎች አክለውም መለስ ሃገሪቱን በምግብ ራሷን አስቺላለሁ በማለት በመገታቱ እናመሰግነዋለን፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ ፍጆታ አትርፌ ለመላው ዓለም የምግብ እህል አቀርባለሁ ወይንም እሸጣለሁ ብሎ ቢናገርስ ይችል አልነበር በማለት የምጸት አስተያየት መስጠታቸውን ዘጋቢያችን በላከልን መልክት ገልጾልናል።

## ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በጠረፋማ ክልሎች ሊዘረጋ ያቀደው አዲስ የቁጥጥር መዋቅር የትጥቅ ቡድኖችን እንቅስቃሴ ለመግታት ያለመ መሆኑ ታወቀ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በጠረፋማ ክልሎች ሊዘረጋ ያቀደው አዲስ የቁጥጥር መዋቅር በአካባቢዎቹ የሚመላለሱ የትጥቅ ቡድኖችን እንቅስቃሴ ለመግታት ያለመ እንደሆነ ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰ ዘገባ አሳይቷል።

አገዛዙ በአራት የጠረፍ ክልሎች "የገበሬ መንደር" የሚባል እና ከቀበሌ ያነሰ የቁጥጥር መዋቅር ለመመስረት መነሳቱን ሐሙስ እለት መዘገባችን ይታወሳል። ይህንንም እቅድ ለማስፈጸም፣ በአዲሱ ለገሰ የሚመራ የወያኔ ባለስልጣናት ቡድን ጥናት የማካሄድ መርሃ ግብር ወስዶ ከሁለት ወራት በፊት ስራ መጀመሩ ታውቋል።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከሰሜን ኢትዮጵያ አጠናቅሮ እንዳስተላለፈው መረጃ፥ ከገበሬ መንደር ምስረታው ጎን ለጎን እየተጠኑ ካሉት ሃሳቦች ውስጥ አንዱ በጠረፍ ላይ ያሉ መንደሮችን ነቅሎ ነዋሪዎቹን ወደ መሃል ማስጠጋት ነው። ለሂደቱ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዘጋቢያችን እንደገለጹት፥ የዚህ እቅድ ዘላቂ አላማ፣ በየክልሎቹ የሚንቀሳቀሱትን ታጣቂ ቡድኖች በጠረፍ ላይ ከሚኖረው ህዝብ ለመለየት እና ህዝቡ ይኖርበት በነበረው አካባቢ ደግሞ ጦሩን ማስፈር ነው።

የገበሬ መንደር ምስረታው ሊካሄድ የታቀደው በአፋር፣ በሶማሌ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ቢሆንም፤ የታቀደውን ስራ እንዲያስፈጽሙ የተመደቡት ግን የትግራይ፣ የኦሮምያ፣ የአማራ እና የደቡብ ክልል ፕሬዚደንቶች እንደሆኑም ከዚህ በፊት መዘገባችን ይታወሳል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# የኢትዮጵያው አስር በመቶ እድገትና ዘጠና በመቶ ድህነት

"የአህዴድ ሰዎች በነጋ በጠባ ልማት ልማት እያሉ ይጨቀጭቁናል እኛ የተረፈን ልማታቸዉ ሳይሆን እርግጫቸዉ ነዉ፤ እንኳን የመኪና መንገድ ወደ ጨረቃ የሚወስድመንገድም ቢሰሩ እኩለነታችን እስካልተረጋገጠ ድረስ እኔ ለነሱ ድምፄን አልሰጥም" **ስሙ የማይታወቅ ኢትዮጵያዊ ገበሬ** ይህ አባባል እዉቁ የብሉምበርግ ጋዜጠኛ ኦሮሚያ ክልል ዉስጥ በአጋጣሚ አግኝቶ የጠየቀዉ የአንድ ገበሬ ብቸኛ ስሜት አይደለም። ወይም አባባሉ የወያኔ ጀሌዎች እንደሚያስወሩት ለስልጣን የቋመጡየጥቂት ግለሰቦች እምነትም አይደለም። አባባሉ የወያኔ ግፍና በደል ያንገፈገፋቸዉ ኢትዮጵያዉያን ሐይማኖት፤ዘርና ፖለቲካ ሳይከፋፍላቸዉ በጋራ የሚያሰሙት ህዝባዊ እሮሮ ነዉ።

ላለፉት 19 አመታት የወያኔ መሪዎች የኢትዮጵያን ህዝብ መታዘብ ከሚችለዉ በላይ ዋሽተዉታል። ዘንድሮማ ዉሸታቸዉ ተዋሽቶ ተዋሽቶ ያለቀባቸዉ ይመስል የራሱን ህዝብ መቀለብ አቅቶት በምዕራባዉያን ድጎማ የሚንፏፏቀደዉን ኤኮኖሚ በእጥፍ ድርብ አደገ እያሉ መቀለድ ጀምረዋል። የሚገርመዉ እነሱ እድገትና ዲሞክራሲ እያሉ ይጨሁበት እንጂ ህዝቡማ የወያኔ ዘረኞች ለራሳቸዉና ለተወለዱበት አካባቢ ጥቅም ብቻ የቆሙ ነጣቂዎች መሆናቸዉን ካወቀ ዉሎ አድሯል። ዘረኛዉ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ በከፍተኛ ፍጥነት አደገ የሚሉት ኤኮኖሚ ስግብግቦቹን የወያኔ ባለስልጣኖች የማይጠረቃ ሆድ ከመሙላት አልፎ የደሃዉን ኢትዮጵያዊ የምግብ ፍጆታ በአንዲት ቁራሽ እንጀራ ማሳደግ እንዳልቻለ ዛሬ አለም ሁሉ የተረዳዉ ይመስላል።ወያኔና ዕድገት ሆድና ጀርባ ናቸዉ። ስለሆነም እድገት፤ ፍትህ፤ እኩልነትና ሠላም የናፈቀን ኢትዮጵያዉያን ሁሉ ያለን አማራጭ ወያኔን ማስወገድ ብቻ ነዉ።

የወያኔ አባላት እንኳን ዋሽተዉ ሰዉ ገድለዉም ቢሆን ተጠያቂነት የሚባል ነገር ስለማያዉቁ ፍርዳቸዉ የበቀል ንግግራቸዉ የጥላቻ ነዉ፤ ደግሞም መታወቂያ ካርዳቸዉ ዉሸት ነዉና ሲዋሹ ዉለዉ ሲዋሹ ቢያድሩ ቅርም የሚላቸዉ አይመስልም። እነዚህ ከሀዲዎች ሲመሽ የሚጨንቃቸዉ ነገ ምን እንዋሻለን የሚል ስጋት ነዉ እንጂ ትናንት የዋሹትዉሸት አይደለም። ለምሳሌ ዘረኛዉ መለስ ዜናዊ የግንቦቱ ምርጫ እለት ረፋዱ ላይ የሮይተር ጋዜጠኛ ምርጫዉን አስመልክቶ የጠየቀዉን ጥያቄ ሲመልስ እንዲህ ብሎ ነበር - "ለሰባት አመታት ኤኮኖሚን በድርብ አኀዝ ያሳደገ ፓርቲ በምርጫ ሲሸነፍ በዓለም ታይቶ አይታወቅም"እዚህ ላይ መሠረታዊዉ ጥያቄ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል ወይም አላደገም የሚለዉ ጥያቄ አይደለም። ይህንንማጥያቄ ኢትዮጵያ ዉስጥ ስራ አጥተዉ አረብ አገር ለባርነት የሚጋዙት እህቶቻችንና የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ የራሱን ሆድ በገመድ እያሰረ ልጆቹን በፈረቃ የሚመግበዉ አባወራ ሳይጠየቁ መልሰዉታል። ለመሆኑ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ለሰባት አመታት በድርብ አኀዝ ያደገዉ ከመቼ እስከመቼ ነዉ?

መቼም መለስ ዜናዊ ሲዋሽ ለነገ የማይል ሰዉ ሆኖ ነዉ እንጂ ለመሆኑ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ የኢትዮጵያን አርሶ አደርና ሠራተኛ ህዝብ በሚያረካ መልኩ ለአንዲት አመት እንኳን በስርአት ያደገዉ መቼ ነዉ? የአለም ባንክንና የመለስ ዜናዊን የራሱን ስታትሰቲክስ ጽህፈት ቤት ያለፉት አስር አመታት አመታዊ ሪፖርት ተመለከትንና አቶ መለስ ለዋሹት ዉሸት እኛ አፈርንላቸዉ እንጂ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚማ ህዝብን በሚጠቅም መልኩ እንኳን ሰባት አመት አንድም ቀን አድጎ አያዉቅም።

እዉነቱ ይዉጣ ከተባለ - በዚህ እንደ "ፄኔ ቢጤ" ዲሪቶ ከዚህም ከዚያም በህዝብ ስም በተሰበሰበ ገንዘብ በሚንቀሳቀሰዉ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ የተጠቀመ የህብረተሰብ ክፍል ቢኖር የኤፎርት ባለቤት የሆነዉ የትግራይ ክልል፤ የወያኔ ባለስልጣኖች፤ ወያኔን የተጠጉ ጥቂት ሆዳሞችና የሼክ አላሙዲን ንብረት የሆነዉ ሚድሮክ ኢትዮጵያ ኩባኒያ ብቻ ናቸዉ። የተቀረዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን እነዚህ የቀን ጅቦች እየበሉ ሲያገሱ ከመመልከት አልፎቤሳቤስቲን ደርሶት አያዉቅም። ባጠቃላይ ዛሬ ኢትዮጵያዉስጥ እንሹራንስ፤ ባንክ፤መንገድና ህንፃ ኮንስትራክሺን፤የህዝብና የጭነት ማመላለሻ፤ የንግድ፤የእርሻና የኢንዱስትሪ ተቋሞችን በባለቤትነት ይዘዉ የሐገሪቱን ጥሬ ሐብት የሚቦጠቡጡት እነዚሁ በዘረኞችና በጥቂት ሆዳሞች የተያዙ ኩባኒያዎች ናቸዉ። ለዚህ ነዉ "ሆድን በጎመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል" እንደሚባለዉ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በፍጥነት እያደገ ነዉ በተባለ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ የሚበላ አጥቶ በችግር የሚጠበሰዉ። በነገራችን ላይ ዛሬ የኢትዮጵያ የእድገት ደረጃ መለስ ዜናዊ ዶላር ባስታቀፉት ቁጥር ጦር እየላከ ከሚያሰቃያትና ለ20 አመት ሙሉ መንግስት ከሌላት ከሶማሊያ አጅግየከፋ ነዉ።

ባለፈዉ ሳምንት ታትሞ የወጣዉ ፋይናንሻል ታይምስ የተባለ ተአማኒነት ያለዉ መጽሔት ኢትዮጵያ ዉስጥ አገዛዙ አለ የሚለዉ እጥፍ ድርብ የኤኮኖሚ ዕድገት ዕርዳታ ለጋሾችን ለማስደሰት ሆን ተብሎ የተቀለለ የቁጥር ክምር ስለመሆኑ ምንም የሚያጠያይቅ ነገር የለም ብሏል። የህንን የአደባባይ ምስጢር ደግሞ ዋሾዉ መለስ ዜናዊም ቢሆን ቢለዉ ቢሰራዉ አልደበቅ ስላለዉ ለመጀመሪያ ግዜ በአደባባይ የኢህአዴግን የቁጥር ማሳደግ ችሎታ በቀጥታ ባይሆንም በተዘዋዋሪ አምኗል።

በያዝነዉ የነሐሴ ወር እጅግ ካስገረሙን ነገሮች አንዱ የመለስ ዜናዊን "እድገት" የሚሉት የወሬ ቱማታ " ጉ . . . ድ" ብለን ሳንጨርስ - የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ ሶፊያን አህመድ "በተስፋ የተሞሉት ቀጣዮቹ አምስት አመታት ኢትዮጵያ በዓለም ፊት ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ በተመጽዋቹነት ስሟ አይነሳም" ብለዉ የተረቱት ተረት ነዉ። አቶ ሶፊያንና ፓርቲያቸዉ እህአዴግ እናደርጋለን ብለዉ ለህዝብ ቃል ከገቡት ነገሮች ሲሶዉን ያክል እንኳን በተግባር የመተርጎም ችሎታ ቢኖራቸዉ ኖሮ የአቶ ሶፊያን መልካም ምኞት አለምን ሁሉ ያስደስት ነበር።በነገራችን ላይ አቶ ሶፊያንአስበዉ ይሆን አዳልጧቸዉ የዛሬ አምስት አመት የተናገሩትን ነገር እሳቸዉ ቢዘነጉትም ተስፋ የተገባለት የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የሚዘነጋዉ አይመስለንም። የ1997ቱ ምርጫ እንዳለቀ አቶ ሶፊያን "በ2015 ዓም ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ጋር ትሰለፋለች" ብለዉን ነበር። የሚገርመዉ የገንዘብ ሚኒስትሩ ይህንን ሲናገሩ ኢትዮጵያ በአለማችን ላይ ከታች ወደ ላይ 4ኛዋ ደሃ አገር ነበረች። ዛሬ ከአምስት የወያኔ የእድገት አመታት በኋላ ኢትዮጵያ ከሁለት የመጨረሻ ደሀ አገሮች ወስጥ አንዷ ናት።እያደገ ሄዶ መካከለኛ ገቢ ካላቸዉ አገሮች ተርታ ያሰልፈናል ብለዉ አቶ ሶፊያን የተናገሩለት የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ቁልቁል ወይም የኋሊዮሽ እያደገ አገራችንን ጭራሽ የመጨረሻዋ ደሃ አገር አሰኝቷታል። ሰሞኑን የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ከተመድ ጋር በመተባበር ባወጣዉ ሰፋ ያለ ጥናታዊ ሪፖርት ላይ ኢትዮጵያ በድህነት ከታች ወደ ላይ ሁለተኛዋ አገር ሆናለች። ድህነታችንና ኋላ ቀርነታችን እጅግ የሚያንገበግበን ቢሆንም እዚህ ላይ ግን በጣም የሚያሳዝነን "ታዳጊዉ የአፍሪካ አኮኖሚ" የተባለለትን ፈጣን ኤኮኖሚ ይዘን ዛሬም ሩጫችን ወደፊት ሳይሆን ወደ ኋላ መሆኑ ነዉ።

መቼም መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ሲሰሩም ሲያወሩም ፀባያቸዉ ዛሬ የገነቡትን ነገ ማፍረስ ነዉ። እንግዲህ ይታያችሁ ማፍረስ - መገንባት ማፍረስ - መገንባት . . . ሃያ አመት ሙሉ! ከሰሞኑ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ ሶፊያን አህመድ ተመፅዋጭነት የሚባል ቋንቋ ከኢትዮጵያ ምድር ይወገዳል ብለዉን ነበር። የሚገርመዉ የአቶ ሶፊያን ንግግር ጋዜጣ ላይ ወጥቶ ገና የታተመበት ቀለም ሳይደርቅ ነዉ መለስ ዜናዊ መጥቶ በቀጣዮቹ አምስት አመታት የተያዘዉ የልማትና ዕድገት ዕቅድ ሙሉ በሙሉ ይፈፀማል ብሎ በእርግጠኝነት መናገር እንደማይቻል የገለፀዉ። የማንን አምነን የማንን እንደምንተዉ ባናዉቅም እንደ መለስ ዜናዊ አባባል ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት አምስት አመታት በተመፅዋቹነት ትቀጥላለች ማለት ነዉ። እኛም አትልፉ ሲለን በአቶ ሶፊያን ልዩ ትዕዛዝ ከመዝገበ ቃላታችን ዉስጥ እንዲፋቅ ያሰመርንበት "ተመፅዋቹነት" የሚለዉ ቃል ለሌላ አምስት አመት ሊሰነብትልን ነዉ። ባጠቃላይ የገንዘብ ሚኒስትሩ የሀገሪቱን ያለ የሌለ ብር ደምረዉ ልመና አብቃ ሲሉን ጠ/ሚኒስትሩ ግን እሳቸዉና ጋደኞቻቸዉ ኪስ የሚገባዉን የገንዘብ ልክ ያዉቃሉና ብር የለም ልመናዉ ይቀጥላል ብለዉናል።

በሌላ በኩል ደግሞ መለስ ዜናዊ ባለፈዉ ሐሙስ ለአገር ዉስጥ ጋዜጠኞች በሰጠዉ መግለጫ ገዢዉ ፓርቲ ኢህአዴግ ኤኮኖሚዉ አደገ የሚለን ከቁጥር ጋር እየተጫወተ መሆኑን አምኖ ይህ የቁጥር ማሳደግ ጨዋታ ከዛሬ በኋላ አይደገምም ብሏል። ለሁሉም መለስ ዜናዊ እንደዚህ ነበር ያለዉ - "መንግስት አነስተኛ የልማት ዕቅድ ይዞ ዕቅዱን መቶ በመቶ አሟልቻለሁ ከሚል ይልቅ ቢያንስ በዕቅድና በሙከራ ደረጃ ትልቅ ነገር አስቦ በተግባር ቢንቀሳቀስ ይሻላል" ከዚህ የመለስ ዜናዊ አባባል የኢትዮጵያ ህዝብ ሚከተሉትን ሁለት ቁም ነገሮች ይረዳል ብለን እናምናለን። በመጀመሪያ አገዛዙ ትልቅ ነገር አስቦ እንደማይንቀሳቀስ ጠ/ሚኒስትር ተብዬዉ በግልፅ ተናግሯል፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አገዛዙ <<የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ>> በእጥፍ ድርብ አደገ የሚለዉ ሆን ብሎ ቁጥሮችን በማሳደግ መሆኑን መለስ ዜናዊ በተዘዋዋሪ ግልፅ አድርጎታል።

አገራችን ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ኃይለስላሴና በደርግ ዘመነ መንግስትም ቢሆን ደሃ አገር ነበረችና ዛሬ ኢትዮጵያ ደሃ ናት ሲባል ብዙ ላይገርመን ይችላል። ሀቁ ግን እንደዚህ ነዉ - ከ80 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ ዉስጥ 90% ወይም 72 ሚሊዮኑ በከፍተኛ ድህነት ዉስጥ ነዉ የሚኖረዉ። 31 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ የቀን ወጪዉ ከ $1.25 ያነሰ ነዉ።49.6 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ በቂ የትምህርት ዕድል አያገኝም። እነዚህ መረጃዎች ደግሞ እኛ የሰራናቸዉ ሳይሆኑ የተ.መ. ድ ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ያጠናቀረዉ ጥናታዊ ዉጤት ነዉ።እዚህ ላይ ጭራሽ ሊገባን ያልቻለ ነገር ቢኖር አገራችን ይህን የመሰለ የድህነት ማጥ ዉስጥ የገባቸዉ በአፍሪካ ዉስጥ ቁጥር አንድ የምግብና የገንዘብዕርዳታ ተቀባይ አገር ሆና ነዉ። እያምጣዉ እንጂ በአንድ አጋጣሚ ለጋሽ አገሮች እጃቸዉን ቢያጥፉ ምን ይዉጠን ይሆን?

በ2002ቱ ምርጫ ዋዜማና ማግስት የኢትዮጵያን ህዝብ ጆሮ ካደነቆሩት የወያኔ ፕሮፓጋንዳዎች አንዱ "የኤኮኖሚ እድገት" የሚባል በእጅ የማይዳሰስ በአይን የማይታይ የዘረኞች ባዶ ጫጫታ ነበር። በትግራይ ተራድኦ (ኤፎርት) ስር የሚገኙትን የመንገድና የህንፃ ኮንስትራክሺን ድርጅቶች ለመጥቀም ሲባል በየቦታዉ የሚገተሩት ህንፃዎችና ተሰሩ የሚባሉት መንገዶች ሰዉ ሳይኖርባቸዉና መኪና ሳይሄድባቸዉ የጥገና እቅድ የሚወጣላቸዉ ጉዶች ናቸዉ። የሚገርመዉ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ በአስተማማኝ ክረምት ከበጋ የሚያገለግሉት መንገዶች፤ ድልድዮችና የመሬት ስር መተላለፊያዎች ጣሊያኖች የዛሬ ሰባ አመት የገነቧቸዉ ናቸዉ እንጂ የወያኔ ነካ ነካ መንገዶችና ህንፃዎችማ ሰኞና ማክሰኞ እየተገነቡ ሐሙስና አርብ ዕድሳት የሚያስፈልጋቸዉ የወያኔን ኪስ ለመሙላት ብቻ የሚሰሩ ስራዎች ናቸዉ። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በድህረ-ምረቃ የትምህርት ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ ከተመረጡ ተማሪዎች ውስጥ ሰማንያ በመቶ የሚሆኑት የአንድ ብሔር ተወላጆች ናቸው የሚል ስሞታ ቀረበ

ባመጧቸው ጥሩ ውጤቶች የተመለመሉ የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን በአዳማ እና በመቀሌ ዩኒቨርሲቲዎች ተሰብስበው ስለ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሲሰበኩ እንደሰነበቱ መጥቀሳችን ይታወሳል።

የግንቦት 7 ድምጽ የአዲስ አበባ ሪፖርተር አጠናቅሮ በላከው ተከታይ ዘገባ እንዳስታወቀው፥ በስልጠናው ፍፃሜ ላይ በሁለቱ የስልጠና ቦታዎች መቶ መቶ ተማሪዎች ለሁለተኛ ዲግሪያቸው ትምህርት እንዲቀጥሉ ተመርጠዋል።

ዘጋቢያችንን ያናገሩት የስልጠናው ተሳታፊዎች ከተመረጡት ውስጥ 80% የሚሆኑት የትግራይ ተወላጆች ናቸው ብለዋል። ተማሪዎቹን ለመምረጥ በስራ ላይ የዋለው መስፈርት ግልጽ እንዳልሆነላቸው እና ሂደቱ በዘር አድሎ ላይ የተመሰረተ ነው ብለው እንደሚያምኑም ተናግረዋል።

የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ተቆጣጥሮ በቆየባቸው ባለፉት ሃያ አመታት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘረኛን ስርአት በማስፈን ከአንድ ብሔረሰብ የተመረጡ ጥቂቶችን ለመጥቀም ሲሰራ እንደቆየ የሚታወቅ ሲሆን፤ እንደዚህ ያሉ ስሞታዎችን መስማትም የተለመደ ሆኗል።

በኢትዮጵያ መከላከያ ሃይል ውስጥ ከስልሳ ቁልፍ የስልጣን መቀመጫዎች ውስጥ 57ቱ በትግራይ ተወላጆች ተይዘው እንዳሉ የግንቦት 7 የጥናትና ምርምር ክፍል ከአንድ አመት በፊት ባወጣው ሰነድ ማጋለጡ ይታወሳል። የኢኮኖሚ እና የትምህርት እድል ስርጭትን በሚመለከትም ከፍተኛ የሆነ የዘር አድሎ እንደሚካሄድ በተለያዩ ጊዜያት ያቀረብናቸው ዘገባዎች አሳይተዋል።

## ግንቦት7 የዘረኛውን አምባገነን መለስ ዜናዊ የ እንነጋገር ጥሪ የተለመደ ቅጥፈት ነው ሲል አጣጣለው

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ የሆነው መለስ ዜናዊ ለአገር ውስጥ ጋዜጠኞች በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ፡ ህገመንግሥቱን ተቀብለው በሰላማዊ መንገድ መንቀሳቀስ እስከ ተስማሙ ድረስ ከማንኛውም ሃይል ጋር ለመደራደር እንደሚፈልግ ገልጾ በሃይል ከስልጣን ሊያባሪሩኝ ነው እያለ ዘወትር ከሚከሳቸው የግንቦት7 እና የ ኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጋርም ለመነጋገር ዝግጁ እንደሆነ መናገሩን ጋዜጣዊ መግለጫውን የተከታተሉ የተለያዩ የዜና አውታሮች መዘገባቸው ይታወቃል።

ይህንን አስመልክቶ የግንቦት 7 ን አቋም እንዲገልጹልን የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ|ር ብርሃኑ ነጋ የወያኔ መሪዎች በተለይም በቅርበት የሚያውቁት መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረበሮቹ የሥልጣን ዕድሜያቸውን የሚያራዝም መስሎ እስከታየቸው ድረስ አደባባይ ላይ ቆሞ መዋሸትን እንደነውር የሚቆጥር ህሊና ስለሌላቸው የሚናገሩትን ወይም ቃል የሚገቡትን ነገር ከምር የሚወስድ ኢትዮጵያዊ የለም ስሉ አጣጥለውታል።

## የአውራምባ ታይምስ ጽ/ቤት . . . (ከገጽ 1 የዞረል)

ታይምስ ማኔጂንግ ኤዲቶር መናገሩን ለጽ/ቤቱ ቅርበት ያላቸው ምንጮች መግለጻቸውም ታውቋል። ፖሊስ ሪፖርት ከተደረገለት ጊዜ እጂግ ዘግይቶ ወደ አውራምባ ታይምስ ጽ/ቤት መምጣቱን፤ ነገር ግን እንኳን የተፈጠረውን አጠቃላይ ችግር መፍትሄ መፈለግ ይቅርና የጥቃቱ ሰለባ የሆነውን የጽ/ቤቱ ዘበኛ ለማናገር ፈቃደኛ ሳይሆን መቅረቱን ዘጋቢያችን ጨምሮ ገልጿል፡፡

የችግሩን ሂደት በቅርበት ሲከታተሉ የነበሩና ስማቸው እንዳይገለጥ የጠየቁ የአይን እማኝ በተለይም ፖሊስ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት አለመተባበሩ እጂግ አሳፋሪና አሳሳቢ እንደሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውም የፖለቲካ ችግር እጂግ እየተወሳሰብ እንደመጣ ተናግረው ከዚህ የአውራምባ ጽ/ቤት ጥቃት በስተጀርባ አዛዥ ሃይል እንዳለ ምንም የማይጠራጠሩ መሆናቸውንም ጨምረው ገልጸዋል።

## የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያሉ ኤርትራውያን . . . (ከገጽ 1 የዞረል)

በሚገኙ አንዳንድ የኢትዮጵያ የገጠር መንደሮች በዘረጋው የቁጥጥር መዋቅር አማካኝነት፣ ገበሬዎች ከሚኖሩበት ቀጠና ውጪ ሲጓጓዙ ለካድሬዎች እንዲያስታውቁ እንደሚያስገድድ ይታወቃል።

በተያያዘ ዜና አንዳንድ ለዝግጅት ክፍላችን እየደረሱ ያሉ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፣ ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የሚኖሩ ኤርትራውያን ስደተኞች ሥም የተለያየ ጥቅማ ጥቅም እየሰበሰበ እንደሆነ ተጋልጦአል። ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸው አንዳንድ ምንጮች እንደምናገሩት የወያኔ ባለሥልጣናት የትግራይ ተወላጅ የሆኑ በርካታ ሰላዮቹን ወደ ስደተኛ ካምፖቹ እያስገቡ ፣ ለኤርትራውያን ስደተኞች በሚሰጠው ዕድል ወደ ምእራብ አገሮች እንዲሄዱ በማድረግ ላይ መሆነቸውን የደረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ወያኔ ባለፈው ሳምንት ኤርትራውያን ስደተኞችን አስመልክቶ ባወጣው መመሪያ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ኮሚሽን ተግባሩን እንደ ቅን በመቁጠር ለወያኔ መሪዎች ምስጋና ማቅረቡ ሌላኛው ወያኔ ከዚህ ርካሽ ተግባር ያገኘው ትርፍ ነው።

## የገቢዎች ሚንስቴር ካቀድኩት በላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረል)

ነጋዴ እንዴት እንደሚዘርፉትና እንደሚያምገላቱትም የሳያል ብለዋል።

የወያኔው የገቢዎች ሚንስቴር የሰጠው መግለጫ ርስ በርሱ ይጋጫል ያሉ ሌላው አስተያየት ሰጪም እንደተናገሩት ባንድ በኩል ህብረተሰቡ ግብር እየከፈለ ያለው ለህግ ተገዢ በመሆኑ ነው እያለ በሌላ በኩል ግን ከግብር ለተሰበሰበው ገቢ ከፍተኛ መሆን አስተዋጽኦ ያደረገው በፍርድ ቤት የተከሰሱ ነጋዴዎችን በማሸነፋችን ነው ማለቱ አሳፋሪ ነው ካሉ በኋላ ፍርድ ቤትም ቢሆን የወያኔውን አገዛዝ ቃል የሚጠብቅ በመሆኑ ፍርዱ ትክክል ነው ወይንም አይደለም ብሎ መናገሩ ትርጉም የለውም በማለት አስተያየታቸውን ቸርሰዋል።

## የኢትዮጵያው አስር በመቶ . . . (ከገጽ 3 የዞረል)

በአገራችን በኢትዮጵያ ታሪክ በአጭር ግዜ ዉስጥ ከፍተኛ የግንባታ ስራ የተሰራበት ወቅት ቢኖር ከ1928 እስከ 1933 የነበሩት አምስት አመታት ናቸዉ። በእነዚህ አምስት አመታት ዉስጥ ጣሊያኖች እየወጉንም ቢሆን የወያኔ ዘረኞች በ20 አመት ከሰሩት ስራ እጅግ የሚበልጥ ስራ ሰርተዋል። ታድያ የኢትዮጵያ ህዝብ ለምን ጣሊያኖችን እጁን ዘርቶ አልተቀበላቸዉም? ከአገራችን ወጣ ብለን የደቡብ አፍሪካን ታሪክ ስንመለከት ደግሞ ከ1900 - 1990 በነበሩት 90 አመታት ዉስጥ በቴክኖሎጂ፤በንግድ፤በእርሻ፤በእንዱስትሪና በወታደራዊ ጥንካሬ ደቡብ አፈሪካን የመሰለ ጠንካራ አገር አፍሪካ ዉስጥ አልነበረም። ደቡብ አፍሪካ የኑክለር ሀይል ባለቤት ነበረች፤ ደቡብ አፍሪካ በአለማችን የመጀመሪያዉ የልብ ቀዶ ጥገና የተካሄደባት አገር ናት። ታዲያ እንደዚህ አይነቷን ሀብታምና በእድገት የገፋች አገር ጥቁር አፍሪካዉያን አምርረዉ የታገሉት ለምንድነዉ? የእነዚህን ሁለት ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ብዙ መጓዝ የሚያስፈልግ አይመስለንም። የጣሊያን ፋሺስቶችያሰኛቸዉን ያክል መንገድና ህንፃ ቢገነቡም የአባቶቻችን የነፃነት ፍላጎት በምንም ያክል ቁሳዊ ኃብት የሚገመት አልነበረምና የጣሊያን ወራሪዎችን አልተቀበሉም። ደቡብ አፍሪካ ዉስጥ ደግሞ ነጮቹ ጥቁሮችን በእኩልነት የማይመለከቱ ዘረኞች ስለነበሩ የደቡብ አፍሪካ ፈጣን የኤኮኖሚ እድገት የጥቁር ደቡብ አፍሪካዉያንን የነፃነት ፍላጎት አልገታዉም። እንግዲህ ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባ ላይእራሳቸዉን የጫኑት ወያኔዎች እንደ ደቡብ አፍሪካ ነጮች ዘረኞች እንደ ጣሊያን ፋሺስቶች ወራሪዎች ናቸዉና የኢትዮጵያ ህዝብ በምንም አይነት ሊቀበላቸዉም ሆነ ሊታገሳቸዉ አይገባም።

ኢትዮጵያ በዕድገት ገስግሳ በአንድ ጀምበር የዛሬዋን አሜሪካ ብታስከነዳ እንኳን ነፃነት፤ፍትህና እኩልነት አገራችን ዉስጥ እስካልተረጋገጠ ድረስ ትግላችን ላፍታም ቢሆን መቆም የለበትም። ነፃነታችንን ገፍፈዉ ምግብና ቤት እየሰጡ ከሚደልሉን ነፃነታችንን ያክብሩልንና ያሰኘንን ምግብና ቤት እኛዉ እንሰራለን። የራበን ነፃነት ነዉ እንጂ ምግብ አይደለም።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሰብዓዊ መብቱንና ነፃነቱን ለድርድር አቅርቦ ወይም በኤኮኖሚ ጥቅም ለዉጦ አያዉቅም። ከመንግስት ተቀዳሚ ተግባሮች አንዱ ኤኮኖሚን ማሳደግና የህዝብን መሠረታዊ ጥቅም ማስጠበቅ ነዉ። እንደዚህ ማለት ግን ኤኮኖሚን ያሳደገ ገዢ ፓርቲ ስልጣን እንደያዘ ዕድሜ ልኩን ይቆያል ማለት አይደለም። የወያኔ ዘረኞች አሳደግነዉ የሚሉት ኤኮኖሚ ደግሞ ታይቶ የማይዳሰስ ምትሀትቢበሉትየማይጠጋ መዐት ነዉ። መለስ ዜናዊ እድገትን በተመለከተ ያልተሰራ ስራ ተሰርቷል፤ ያልተጀመረ ነገር አልቋል እያለ በዋሸ ቁጥር የሚያምኑትን ፈረንጆች ቢያሞኝም - ሺ ዉሸት ቢከመር አንድ አዉነት አይወጣዉምና ዛሬ ሳይወድ በግድ ዉሎ ያደረ ዉሸቱን ማስተባበል ጀምሯል። ኮንዶሚኒየም በአስርሺዎች ተሰራ እየተባለ የበረንዳ አዳሪዉ ቁጥር በእጥፍ መጨመሩና የእርሻ ምርት በእጥፍ አደገ እየተባለ የረሀብተኛዉ ቁጥር በፍጥነት ማደጉ በዛሬዋ ኢትዮጵያ ዉስጥ ደልቶት የሚኖረዉ መለስ ዜናዊ “ወርቃማዉ” እያለ የሚጠራዉ ጥቂት የህብረተሰብ ክፍል ብቻ መሆኑን ዘረኛዉ መለስ ዜናዊን በአንቀልባ የተሸከሙት ምዕራባዉያን ወዳጆቹ ጭምር የተረዱት ይመስላል።አንዳንዶቻችን ወያኔን ከሚገባን በላይ ሰለለመድነዉ እንዳሳደግነዉ ዉሻ አብሮ መዝለል ይቃጣናል፤ አንዳንዶቻችን ደግሞ ወያኔ ቢከፋም ኢትዮጵያን ቀይሯታል የሚል ቅዠት ዉስጥ የገባን ይመስላል። ከእነዚህ ከሁለቱም ያልሆንነዉ ደግሞ እነ እገሌ ናቸዉ እንጂ አገር አጥፊዎች መለስ ዜናዊማ ምን አጠፋ “ይቀጥል” የሚለዉን የሠለሞን ተካልኝን ዘፈን የወደድነዉ ይመስላል። ይህንን ሌሎቹ ናቸዉ እንጂ መለስ ዜናዊማ ከዚህ በላይ ምን ያድርግየሚለዉን የነፈሰበትተረት ስንሰማ አንድ ቆየት ያለ ተረት ትዝ አለን - አንድ እንቅልፍ ባይናቸዉ አልዞርያለ ቄስ በጧት ተነስተዉ ከወዲህ ወዲያ ሲሉ - ገበሬዉ በሬዎቹን ፈትቶ ብሳና ስር ቁጭ ብሎ ዉኃ ሲጠጣ አዩትና ጠጋ ብለዉ - አያ እገሌ ብሳና ይሸታል እንዴ ብለዉ ይጠይቁታል። ገበሬዉ ከተቀመጠበት ተነሳና . . . ብሳና የሸታል! ዛፎቹን ሁሉ መሽተት ያስተማራቸዉ ማን ሆነና ነዉ ብሎ መለሰላቸዉ። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ዛሬ ጥያቄዉ ኤኮኖሚዉ አደገ ወይም አላደገም ወይም ከመለስ ዜናዊና ከስብሀት ነጋ ማን ይሻላል አይደለም። መለስና ስብሀት ምንም የሚመረጥ ነገር የላቸዉም። ሁለቱም መነቀል ያለባቸዉ ብሳናዎች ናቸዉ። እነዚህ ሁለት ሰዎች ወይም እነሱ የሚመሩት ህወሀት የሚባል ድርጅት ከአገራችን እስካልተነቀለ ድረስ ትንሽ ቆይቶ ኢትዮጵያ ዉስጥ እንኳን ኤኮኖሚዉ ዛፍም አያድግም። ምርጫችን አንድ - አንድ ብቻ ነዉ። እሱም ነፃነት ነዉ። ነፃነት ደግሞ የብዙኋን ምርጫ ነዉና የሚረጋገጠዉበብዙኋን ትግል ነዉ።


### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ
### የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



### ውድ አንባቢዎቻችን

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org